
## እግዚአብሔር ልጅ አለውን?

- እግዚአብሔር ልጅ አለውን?
- እግዚአብሔር ልጅ የሰጠችው ሚስት ነበረውን?
- ይህ ማለት እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ነው ማለት ይሆን?

የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዐል (ገና) እያከበርን ባለንበት ወቅት በአንዳንድ ወንድሞቻችን ልቡና ውስጥ ሞልቶ ተርፎ የሰማነውን ተመመላሽ ጥያቂዎች መልስ ማዘጋጅት ወደድን። በተመሳሳይ ርዕስ ጽሁፋቸው ተሰናድቶ ያገኘነውን  አባ ታድሮስ ማላቲ አዘጋጅተው  ቅ/ሚናስ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ ያቀረበችውን ቤተ ፍቅር ዘአቢሲኒያ እንደተረጎመው እንዲህ ቀርቧል። እግዚአብሔር ልባችንን ይዳብሰው ይባርከን።



እግዚአብሔርን በቁስ አካላዊ እይታ መመልከት አግባብ አይሆንም ይላሉ አባ ታድሮስ ስለዚህ ርዕስ ሲጽፉ። እርሱ ሰው አይደለም ወይም ሌላ ዓይነት አንዳች ፍጡር አይደለም። የአባትና ልጅ የሚለው አገላለጽ እግዚአብሔር ተጋብቶ ሌላ አማልክ ወለደ ማለትም አይደለም። እግዚአብሔር ጾታ የለውም።

**አባት ልጁን ወለደ ስንል ፀሐይ ጨረሯን እንደወለደችው ማለት ነው። ወይም እንደሰው ልጅ ነፍስ መወለድ ያለ እና ነጸብራቅን ከብርሃን የማግኘት ያለ ምክንያት ነው።**

ልጁ ከብርሃን ብርሃን እንደሚወጣ ወጣ። ሻማ በለኮስህ ጊዜ ከሻማው ብርሃን ተነስተህ ይህ ብርሃን የዚኛው ልጅ ነው ትላለህ- ምንም’ኳ ሁለቱም አንድ ብርሃን ቢሆኑም።

http://www.ermiastizazu.wordpress.com

ይህን ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ማጣቀሻዎች በመውሰድ የበለጠ ማብራራት ይቻላል።

**፩.** ቅዱስ መጽሐፍ ልጁን (ወልድን) "ቃል" ወይም "መለኮታዊ ቃል-Logos" በማለት ይጠራዋል። ይሄ ማለት የአእምሮ ነባቢ ቃል (uttered mind) ወይም የአመክንዮ መገለጫ (logical utterance) ማለት ነው። እርሱ የእግዚአብሔር ጥበብ ተብሎም ይጠራል። 'ወልድ' እና 'የአእምሮ ነባቢ ቃል' በሚለው በሁለቱ ቃላት መሃከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ወልደ አብ ብሎ እርሱን በመጥራት ከአብ የተወለደ ልጅ እንደሆነ ያረጋግጥልናል።

አንድነታቸውንም ሲያረጋግጥም 'መለኮታዊ ቃል' ተብሎም ይጠራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሁለት ማንነትን (two being) ለሰው መጥቀስ አይቻለንም። ምክንያቱም ሰው ውስጣዊ ቃላት ያሏት ነፍስ ያለው ነውና ሁለት መሆንን ለሰው ተግባራዊ መሆን አይቻልም።

ስለዚህም የእርሱን ልጅነት ከመንፈሳዊ እይታ በመነሣት መመርመር ይገባል። ቅዱስ አትናቴዎስ እንዲህ ብሏል "ደግመን አሁንም እንላለን። ይኸውም የመለኮታዊ ልደትን ከሰዎች ልደት ጋር ማነጻጸር አስፈላጊ አይደለም። ወልድን የእግዚአብሔር ክፍል አድርገን ማሰብ አይቻለንም። እንዲሁም መለኮታዊ ልደት ምንም ዓይነት ስሜት ቢሆን'ኳ ማንኛውንም ስሜት አያካትትም። ሰዎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ይወልዳሉ። ግና እግዚአብሔር እንደዚያ አይደለም። እግዚአብሔር ከክፍሎች የተዋቀረ አይደለምና፥ መለወጥ የለበትም። እንዲሁም ወልድ የአብ ክፍሉ እንዲለይ ወይም የተቀየረ እንዲሆን አላደረገውም። ይህ በግልጽ ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ተቀምጧል። የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ነው። ወልድም የእግዚአብሔር ቃልና ጥበብ ነው። ቃል ወይም ጥበብ አይፈጠርም እንዲሁም እርሱ የእግዚአብሔር ክፍል አይደለም። እርሱ መራባት የሚችል ትውልድ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም አገላለጾች ይገኛሉ።

ስለልጁ (ወልድ) ሲናገር ትክክለኛውን ተፈጥሯዊ ልደት የሆነው የእርሱን ተፈጥሮ ሲያረጋግጥ በተመሳሳይ ሰዓት ከሰዎች ልደት ጋር ገራ አንጋባም። እርሱ ቃል፣ ጥበብ፣ ነጸብራቅ ተብሎ ይጠራል። በዚህም የእርሱ ልደት እንዳልተቀየረ ያስተምረናል። የእርሱ ልደት ዘላለማዊ የእግዚአብሔርነት ነው።

**፪.** ለምን ወልድ ተብሎ ተጠራ?

በእግዚአብሔር እና በመለኮታዊ ቃል መሃል ያለው ግንኙነት በእርግጠኝነት ከተገደበው መረዳታችን በላይ ነው። 'ልጅ' ወይም 'አንድያ የተወለደ ልጅ' የሚለው አገላለጽ በራሳችን አገላለጽ ለመረዳት እንችል ዘንድ እንዲረዳን ነው። እርሱ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ ሲሆን እርሱም በተፈጠሮ ከእርሱ ጋር አንድ ነው። ስለዚህም እኛን በተዋሃደ ጊዜ ልጅነቱን በጸጋ ውስጥ እንደ መለኮታዊ ነጻ ሥጦታ ተደሰትንበት።

ይሄን ስያሜ ዋጋ የምንሰጥበት ምክንያት በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር የሸለመን ዘላለማዊ ሥጦታ አግኝተንበታልና ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከልጁ ጋር ተዋሃድን እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ሆንን።


**፫.** እግዚአብሔር በንግስና ዙፋን ላይ ተቀምጧል። ይናገራል፣ ይሰማል፣ ያያል ተብሏል። ምንም'ኳ ለመቀመጥ የሚሆን አካል (ለመስማት ጆሮ፣ ለማየት ዐይን) ባይኖረውም ቅሉ።

እግዚአብሔር እነዚህን ችሎታዎች የሚያደርጋቸው እኛ ከምናደርገው በጣም በተለየ መንገድ ነው። ስለዚህም ልጁ በጣም የተለየ መሆኑ እኛ ሰዎች ለሰውልጅ ካለን እይታ እጅጉን የበለጠ ሊሆን አይችልምን? ራሱ እግዚአብሔር እንዲህ አውጇል "የምወደው ልጄ ይህ ነው" ማቴ ፫፥፲፯ እንዲሁም ሊቀ ካህናቱ እርሱን ሲጠይቀው "የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን?" ክርስቶስም እንዲህ መልሷል "እኔ ነኝ!" ማር ፲፬፥፷፩,፷፪

ሰው የመሆኑን ብስራት ያወጀው መልአክ እንዲህ ብሎታል "የታላቁ ልጅ" ሉቃ ፩፥፴፪ እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ ማንም እንዲህ ማለት አይችልም "ማንም በእኔ ካልሆነ በቀር ወደ አብ አይመጣም" ዮሐ ፲፬፥፮ "እኔን ያየ አብን አይቷል" ዮሐ ፲፬፥፱

http://www.ermiastizazu.wordpress.com

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእርሱና [በወልድ] በሌሎች ሁሉም ነብያት መሃል ያለውን ልዩነት በግልጽ ሲያስቀምጥ እንዲህ ብሏል "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን"




**፬.** የልጁ ዘላለማዊ ልደት የእግዚአብሔርን ተፈጥሯዊ ፍቅር ገለጸው። እንዴት ብትሉ (ምክንያቱም) ማለቂያ [ስፍር] ስለሌለው ፍቅር ልጅን ወልዶ ፍጹም አንድ ዓይነት የሆነ መለኮታዊ ባህርይ ከልጁ ጋር ተጋራ። ከእርሱም ጋር አንድ ሆነ። ፍጹም የሆነውን ራሱንና የራሱን ተፈጥሮ በመስጠቱ የእርሱ ፍቅር የማይነጻጸር ነው። ይሄንን የማይነጻጸር ፍቅር ለእኛ የተገለጠልንና ያወቅነው እኛ ልንገነዘበው በሚቻለን መንገድ ነው።

**እግዚአብሔርን ከፈጠራቸው አርቆና ለያይቶ የሚያስቀምጠውን ሰዋዊ መሠረተ ሀሳብ ይህ ልዩ ልደት አጠፋው፥ እርሱ መስጠት ይችላልና።**

እያንዳንዱ ነገር ወይም ፍጥረት የግድ አንድ ነገር ማምረት [መስጥት] ይኖርበታል። እሳት ብርሃንን እና ሙቀትን ይወልዳል። የቁስ አካሎች ራዲዮ አክቲቭ አካል የአቶሚክ ኃይልን ይፈጥራል። ለሰው ልጅ አዕምሮም ተመሳሳይ ሁኔታን ማስቀመጥ ይቻላል። ይኸውም ሃሳቦችና አስተሳሰቦች ከሰው አዕምሮ ይመነጫሉ፥ ይወለዳሉ። **ስለዚህ እግዚአብሔርን መስጠት የማይችል አካል አድርጎ መግለጽ የማይቻል ይሆናል። የብርሃናት ብርሃን፤ የክብር ነጸብራቅ የሆነውን ቃል እርሱ አመጣው። ለዚህም ነው ሐዋረያው ቅ/ጳውሎስ እርሱም 'የክብሩ መንጸባረቅ፤ የባህርዩ ምሳሌ' በማለት ስለ እርሱ የገለጸው (ዕብ ፩፥፫)** ብርሃንን ያለ ነጸብራቅ ማሰብ የማይቻል ነው። በእውነት ብርሃንን የማይሰጥ ብርሃን ጨለማ ነው።

አባቱ [እግዚአብሔር አብ] ያለ ልጁ የኖረበት [ከዘመናት አስቀደሞም ቢሆን] ቅንጣት ጊዜ የለም። እናም እግዚአብሔር መስጠት አይችልም የሚለውን ሃሳብ መቀበል አንችልም። ፀሐይ ያለ ጨረርና ሙቀቷ መኖር እንደማትችለው አባቱም ያለ ልጁና ከእርሱ ከሰረፀው መንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ብቻውን ሁኖ አያውቅም።

[ይህን የእግዚብሔርን በልጁ ሰው የመሆን ምስጢር ጽሑፍ ከአባቶቻችንን አንደበት ጨልፌን እናብቃ]

### ቅዱስ የአሌክሳንድሪያ ዲዮናሲዮስ

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ጽፏል "የክብሩ መንጸባረቅ፣ የባህርይ ምሳሌ [. .]" (ዕብ ፩፥፫) "እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው" (ቆላ ፩፥ ፲፭) ልክ ስንናገር የሚወጣው ቃል የማይታየው አዕምሮ ምሳሌ እንደሆነው። ነገር ግን የብርሃን ነጸብራቅ ዘላለማዊ ነው ስለዚህም ልጁ ራሱም በእርግጠኝነት ዘላለማዊ ነው። ብርሃን ሁልጊዜ እንዳለ ካየን ነጸብራቁም ምንግዜም አብሮት እንዳለ ግልጽ ነው። የነጸብራቁ መኖር የብርሃኑን መኖር እንደሚያመለክተው። ስለዚህም ብርሃን የማይሰጥ ብርሃን አይኖርም። ዘላለማዊ ነጸብራቅ በፊቱ ያበራል ከእርሱ የተወለደውም ሁልጊዜ በእርሱ መኖር ያበራል። እንዲህ እንደተባለ "እለት እለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፥ በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ (ምሳ ፰፥፴) ስለዚህም አባቱ እንዲሁም ልጁ ዘላለማዊ ነው። ምክንያቱም እርሱ የብርሃናት ብርሃን ነውና።

### ሐዋርያው አባ አትናቴዎስ

አንዳንዶች እንደሚሉት የእግዚአብሔር ተፈጥሮ በራሱ ፍሬያማ አይደለም ወይም እክል አለበት ካልን እርሱ ብርሃን እንደማይሰጥ ብርሃን ወይም እንደ ደረቀ ምንጭ ነው ማለት ይሆናል። የእርሱ ፍጥረታት የሚቻላቸው ሆነው ግና የእርሱን ተፈጥሮ ከደው ስለ እሱ ሥልጣን ሲያወሩ አያፍሩምን?

### ኦሪገን

ስለብርሃን ከእግዚአብሔር አብ ሌላ ምን ልናስብ እንችላለን? ከእርሱ ጋራ የሚኖር የእርሱ ነጸብራቅ (ዕብ ፩፥፫) አይደለምን? ብርሃንን ያለ ነጸብራቅ ማሰብ ፈጽሞ የሚቻለን አይደለም። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ወልድ ልጅ ያልሆነበት ጊዜ አልነበረም ማለት ነው።

**አባ ታድሮስ ማላቲ አዘጋጅተው ቅ/ሚናስ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ ያቀረበችውን ቤተ ፍቅር ዘአቢሲኒያ እንደተረጎመው ታኅሳስ ፳፻፰ ዓ.ም**

http://www.ermiastizazu.wordpress.com